# *እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

## **ሕዋሶቻችንን በሥራ ማስለመድ** (getting our senses exercised by reason of use)

## ክፍል ሦስት: አንደበት / ንግግር

**ዕብ** 5: 11-14
ስለ እርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፥ ጆሮቻችሁም ስለ ፈዘዙ በቃል ልንተረጕመው ጭንቅ ነው። ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም። ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው (have their senses exercised by reason of use) ለፍጹማን ሰዎች ነው።

**በአዲሱ መደበኛ ትርጉም**

**በአምላክ ስለለመጽናናት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ**
11 ስለዚህ ጉዳይ የምንናገረው ብዙ
ነገር አለን፤ ነገር ግን ለመማር ዳተኛ ስለ
ሆናችሁ ለማስረዳት አስቸጋሪ ነው።
12 በዚህ ጊዜ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገ
ባችሁ፣ ገና የእግዚአብሔርን ቃል የመጀ
መሪያ ትምህርት የሚያስተምራችሁ ሰው
ያስፈልጋችኋል፤ የሚያስፈልጋችሁም ጠን
ካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ነው። 13 ወተት
የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለሆነ፣ ከጽድቅ
ትምህርት ጋር ገና አልተዋወቀም። 14 ጠንካራ
ምግብ ግን መልካሙን ከክፉው ለመለየት
ራሳቸውን ላስለመዱ፣ ለበሰሉ ሰዎች
ነው።

---

ብዙ ጊዜ ምናልባት ለብዙዎቻችን ስለአንደበት የሚመጣልን ጥቅስ “አንደበት እሳት ነው: የፍጥረትን ሩጫ ያቃጥላል” የሚለው ሊሆን ይችላል። ሆኖም...

**ምሳ** 18:20-21
20 የሰው ሆድ ከአፉ ፍሬ ይሞላል ከንፈሩም ከሚያፈራው ይጠግባል። 21 ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ (in the power of the tongue) ናቸው፤ የሚወድዱአትም ፍሬዋን ይበላሉ።

20 ሰው በአንደበቱ ፍሬ ሆዱ ይጠግባል፤
በከንፈሩም ምርት ይረካል።
21 አንደበት የሞትና የሕይወት ኀይል
አላት፤
የሚወዷትም ፍሬዋን ይበላሉ።

**“ሰው የዘራውን ያንኑ ያጭዳል” እንደሚለው ቃል ይህ ሙሉ cycle ነው!**

ከደህንነታችን ጀምሮ የምንናገረው (Confess የምናደርገው) ቃል ምን ያህል ስፍራ እንዳለው ብዙ አማኞች አያስተውሉም::
**ሮሜ** 10:9
ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና፤

ክርስትናን ሃይል አልባ ካደረጉት ነገሮች አንዱ በአማኝ ህይወት ውስጥ እ/ር ያስቀመጠው ሃይል በብዙ ሰዋዊ/ሃይማኖታዊ ት/ቶች ምክንያት መገለጥ አለመቻሉ ነው:: አስተምህሮዎቻችን ክርስቶስ የእ/ርን ሥራ በምድር እንዲሰራ ባስቻሉበት ደረጃ እኛን ሊያስታጥቁን ካልቻሉ ችግር አለባቸው ማለት ነው፤ እኛም ጻፎችና ፈሪሳውያን ከተነቀፉበት ሃይል አልባ ሃይማኖታዊ ምልልስ ባልተሻለ ሕይወት ውስጥ ነን ማለት ነው::

አስቀድሞ እ/ር ሰውን በፈጠረ ጊዜ በምድር ላይ በሚሆኑ ነገሮች ሁሉ ላይ ሰውን ባለሥልጣን አድርጎት ነበር:: ምንም እንኳን ሰው በውድቀት ይህንን ክብር ያጣ ቢሆንም በክርስቶስ በኩል ግን ዳግም በመፈጠር ሰው እንደቀድሞ በተፈጠረ ነገር ሁሉ ላይ የበላይ እንዲሆን እ/ር ማሰቡን በተግባር አሳይቶናል::
ለዚህ ጌታ በምድር የሠራቸውን መመልከት በቂ ነው፦
በነገር ሁሉ ክርስቶስን ልንመስል ተጠርተናል ሲባል፦ በባህሪይና በአመለካከታችን (በሃሳባችን) ብቻ ሳይሆን የእ/ርን ሃይል በመግለጥ ጭምር እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ተገልጿል:: “ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ” (ዮሐ 1:8) “እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል” (ዮሐ 14:12)

# *እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

በምድር ሊሆን ላለው ነገር መንፈሳዊው አለም መንገድ (access) ለማግኘትና ርምጃ ለመውሰድ ሁልጊዜ በተጠንቀቅ ነው (መልካሙም ክፉውም)::

**ማቴ 18:18**
18 እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም
የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።19 ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር
በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።
20 ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።

እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ። ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል። (ማር 11:23)

## የቃሉ ምስክሮቻችን

**የእስራኤል ልጆች**
ዘኁ 14: 27-31
<<የሚያጕረመርምብኝን ይህን ክፉ ሕዝብ እስከ መቼ እታገሣዋለሁ? በእኔ ላይ
የሚያጕረመርሙትን የእስራኤልን ልጆች ማጕረምረም ሰማሁ። (ከቁ 1- 4) እንዲህ በላቸው።
እኔ ሕያው ነኝና በጆሮዬ እንደ ተናገራችሁት እንዲሁ በእውነት አደርግባችኋለሁ፥ ይላል
እግዚአብሔር 29 በድኖቻችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ የተቆጠራችሁ ሁሉ፥ እንደቁጥራችሁ
ከሀያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነ ሁሉ፥ እናንተ ያጕረመረማችሁብኝ፥30 ከዮፎኒ ልጅ
ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በቀር በእርስዋ አስቀምጣችሁ ዘንድ እጄን ዘርግቼ ወደ
ማልሁላችሁ ምድር በእውነት እናንተ አትገቡም።

ይህ የሆነው እ/ር የሰውን ድካም የማይረዳ ጨካኝ ገዢ ስለሆነ ሳይሆን ይህ ጽኑ የቃሉ ሥርዓት ስለሆነ ነው፦ "ሞትና ሕይወት በምላስ እጅ ናቸው" (ምሳ 18:20) እንደሚለውና "በአፍህ ቃል ተጠመድህ፤ በአፍህ ቃል ተያዝህ" (ምሳ 6:2) እንደሚለው ማለት ነው::

**ካሌብና ኢያሱ**
ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኘና። ማሸነፍ እንችላለንንና እንውጣ፥ እንውረሰው አለ።
ከእርሱ ጋር የወጡ ሰዎች ግን፦ በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ሕዝብ ላይ መውጣት
አንችልም አሉ። 32 ስለ ሰለሉአትም ምድር ክፉ ወሬ ለእስራኤል ልጆች አያወሩ። እኛ ዞረን (1)
የሰለልናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ምድር ናት በእርስዋም ዘንድ ያየናቸው ሰዎች
ሁሉ ረጃጅም ሰዎች ናቸው። 33 በዚያም ከኔፊሊም ወገን የሆኑትን ኔፊሊም፥ የዔናቅን ልጆች፥
አየን እኛም (2) በዓይናችን ግምት እንደ አንበጣዎች ነበርን፥ (3) ደግሞም እኛ በዓይናቸው
ዘንድ እንዲሁ ነበርን አሉ።

**ዘኁ 14: 7-9**
ምድርን ከሰለሉት ጋር የነበሩት የነዌ ልጅ ኢያሱና የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ልብሳቸውን ቀደዱ 7
ለእስራኤልም ልጆች ማኅበር ሁሉ። ዞረን (1) የሰለልናት ምድር እጅግ መልካም ናት። 8
እግዚአብሔርስ ከወደደን ወተትና ማር ወደምታፈስሰው ወደዚች ምድር ያገባናል እርስዋንም
ይሰጠናል። 9 ነገር ግን በእግዚአብሔር ላይ አታምፁ (2)እንደ እንጀራ ይሆኑልናልና የምድሪቱን
ሰዎች አትፍሩ (3) ጥላቸው ከላያቸው ተገፍፎአል፥ እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር ነው
አትፍሩአቸው ብለው ተናገሩአቸው።

ከዚህ ክፍል ማየት እንደሚቻለው "ሙያ በልብ ነው" እዚህ ጋር አይሰራም!

31 ምርኮኛ ይሆናሉ ያላችኋቸውን ልጆቻችሁን እነርሱን አገባቸዋለሁ፥ እናንተም የናቃችኋትን
ምድር ያውቃሉ።

# *እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

**በግለሰቡ ብቻ ሳይሆን በአገር ደረጃ እንኳን የእ/ር ሰዎች ቃል ሃይል እንዳለው፡-**

**ኢያሱ 10: 8፣12-14**
**እግዚአብሔርም ኢያሱን፦ በእጅህ አሳልፌ ሰጥቼአቸዋለሁና አትፍራቸው ከእነርሱም አንድ ሰው የሚቋቋምህ የለም አለው።**
**12 እግዚአብሔርም በእስራኤል ልጆች እጅ አሞራውያንን አሳልፎ በሰጠ ቀን ኢያሱ እግዚአብሔርን ተናገረ በእስራኤልም ፊት እንዲህ አለ፦ በገባዖን ላይ ፀሐይ ትቁም፥ በኤሎንም ሸለቆ ጨረቃ 13 ሕዝቡም ጠላቶቻቸውን እስኪበቀሉ ድረስ ፀሐይ ቆመ፥ ጨረቃም ዘገየ። ይህስ በያሻር መጽሐፍ የተጻፈ አይደለምን? ፀሐይም በሰማይ መካከል ዘገየ፥ አንድ ቀንም ሙሉ ያህል ለመግባት አልቸኰለም።**

12 እግዚአብሔር አሞራውያንን ለእስራኤል አሳልፎ በሰጠባት ዕለት፣ ኢያሱ እግዚአብሔርን በእስራኤል ፊት እንዲህ አለው፤
"ፀሐይ ሆይ፤ በገባዖን ላይ ቁሚ፤
ጨረቃም ሆይ፤ በኤሎን ሸለቆ ላይ ቀጥ በዪ፤
13 ስለዚህ ሕዝቡ ጠላቶቹን እስኪበቀል ድረስ፣
ፀሐይ ባለችበት ቆመች፤
ጨረቃም አልተንቀሳቀሰችም::
ይህም በያሻር መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል::
ፀሐይ በሰማዩ መካከል ቆመች፤ ለመጥለቅም ሙሉ ቀን ፈጀባት:: 14 እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማበት እንደዚያ ያለ ዕለት ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ አልነበረም፤ እግዚአብሔር ለእስራኤል ተዋግቶ ነበርና::
15 ከዚያም ኢያሱ ከመላው እስራኤል ጋር ጌልገላ ወዳለው ሰፈር ተመለሰ::

**1ነገ 17፣ 1**
**1፣ በገለዓድ ቴስቢ የነበረው ቴስብያዊው ኤልያስ አክዓብን። በፊቱ <u>የቆምሁት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን! ከአፌ ቃል በቀር</u> በእነዚህ ዓመታት ጠልና ዝናብ አይሆንም አለው።**

## *ምን እንናገር?*

1) *ቃሉ ናችሁ ያለውን ሁሉ እንደሆንን*
2) *እ/ር በቃሉና በመንፈሱ ሰጥቻችኋለሁ ያለውን ሁሉ እንደሰጠን*
3) *እ/ር በእኛ አደርጋለሁ ያለውን ሁሉ ሊያደርግ እንደሚችል / እንደሚያደርግ*

***ምናልባት አንዳንዶች ይህንንማ ሁሌ እናደርጋለን ይሉ ይሆናል:: እውነታው ግን ሌላው ቀርቶ "ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው" (2ቆሮ 5:17) የሚለውን የመጀመሪያ ቃል እንኳን ከልቡ አምኖ በድፍረት አዲስ ፍጥረትነቱን የሚያውጅ "አማኝ" ስንት ነው? - ራሱን አንድ ይቅር የተባለ ምስኪን ደካማ ሃጢያተኛ አድርጎ ከማየት ይልቅ - ቤተክርስቲያንም ራሷን ዛሬም እንደሚንገዳገዱና በሃጢያት የሚወድቁ አባላት እንዳሏት ተቋም ከማየት ይልቅ ማለት ነው::***

***ሌሎች ደግሞ ገና ያልሆነውን እንዴት ነን እንላለን ሊሉ ይችላሉ:: እንዲህ ያለ "ትህትና" የለም::***

## **እንዴት እንናገር?**

***የልባችንን ፈቃድ? ምኞታችንን? <u>አይደለም!</u>***

*መዝ* (116):1
*"አመንኩ ስለዚህም ተናገርኩ"*
*በእምነት - እምነት ምድርን ከሰማይ (ወይንም አካላዊውን ከመንፈሳዊው) የሚያገናኝ ድልድይ ነው ካልን፣ በእምነት የምንናገራቸው ቃሎች ደግሞ የድልድዩ መስሪያ አካላት ወይንም ድንጋዮች ናቸው::*

*እግ/ራዊ ለውጥንና ተሃድሶን* (1)*በግል ሕይወታችን በቤተሰባችን እንዲሁም ባለንበት ምድርና በምድራችን ለማምጣት* (2) *ሆኖ እስከምናየው ድረስ* (3) *ከሁኔታዎች በተቃራኒ* (against the odds) *እንናገራለን!*

- *በራሳችን ላይ*
- *በትዳር ጓደኞቻችን ላይ*
- *በልጆቻችን ላይ*
- *በቤተክርስቲያን ላይ*
- *በሥራችን*
- *በአገልግሎታችን…*

## *እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ*

**ዘዳ** 30:14፤15
14፤ ነገር ግን ታደርገው ዘንድ ቃሉ በአፍህና በልብህ ውስጥ ለአንተ እጅግ ቅርብ ነው። 15
ተመልከት፤ ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ።

*ስለዚህ ስንፍናን እንዳንናገር ለአንደበታችን ዘበኛን ማቆም ብቻ ሳይሆን መልካምን ዘር / የእግዚአብሔርን ቃልን/ መዝራትን ልናሰለጥነው ይገባል!!*

### በሚቀጥለው ት/ት ስለመስማት እንመለከታለን::

### ተጨማሪ

**ኢያሱ** 1:7-
7፤ ነገር ግን ጽና፥ እጅግ በርታ፤ ባሪያዬ ሙሴ ያዘዘህን ሕግ ሁሉ ጠብቅ፥ አድርገውም፤
በምትሄድበትም ሁሉ እንዲከናወንልህ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል።
8፤ የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ
በቀንም በሌሊትም አስበው፤ የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።
9፤ በምትሄድበት ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና ጽና፥ አይዞህ፤ አትፍራ፥
አትደንግጥ ብዬ አላዘዝሁህምን?

**ማቴ 8:7-10**
ኢየሱስም፦ እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ አለው። የመቶ አለቃውም መልሶ፦ ጌታ ሆይ፥ በቤቴ ጣራ ከታች ልትገባ አይገባኝም፤ ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል። እኔ ደግሞ ለሌሎች ተገዥ ነኝና፥ ከእኔም በታች ጭፍራ አለኝ፤ አንዱንም። ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም። ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም። ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል አለው። ኢየሱስም ሰምቶ ተደነቀና ለተከተሉት እንዲህ አለ፦ እውነት እላችኋለሁ፥ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም።
**ቁ 13**
ኢየሱስም ለመቶ አለቃው። ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ።

**ኤር** 1:12

### ትንሽ መሪ ትልቁን መርከብ ግን የምታንቀሳቅስ!
### ትንሽ spark ግን ከተማን ሊያጠፉ የሚችል እሳት የምትቀሰቅስ!